የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: መስከረም 20 2017

ቁጥር/REF NO: 8/256/761/17

ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች

**ባሉበት**

ጉዳዩ፡- **የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ትግበራን ይመለከታል**

ትምህርት ሚኒስቴር ከማስተርካርድ ፋውንዴሽን በተገኘ ድጋፍ ከአሪዞና ስቴት ዩኒቨርሲኢቲ እና ከሻያሾኔ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ጋር በመተባበር eLearning for Strengthening Higher Education (e-SHE) የተሰኘ ፕሮግራም አተገባበርን በተመለከተ በቁጥር 8/256/7M2/16 ነሐሴ 07 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መግለጹ ይታወሳል። ደብዳቤው ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጠውን "Student Success Suit (SSS)" ኮርስ ከመደበኛ ትምህርቶች ጋር እኩል ትኩረት ተሰጥቶት ሁሉም ተማሪዎች በተያዘው የትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ወር ውስጥ ስልጠናውን ወስደው እንዲያጠናቅቁ አቅጣጫ አስቀምጧል።

በዚህ መሠረት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ከፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ጋር በመተባበር ስታከናውኑ ቆይታችኋል። ስለሆነም እስከ አሁን ድረስ ትምህርቱን ላልወሰዱ ሁሉም ተማሪዎች የተጠቀሱትን ኮርሶች ማለትም በቀጣይ ለአንደኛ ዓመት ተማሪዎች የተዘጋጁትን ኮርሶች ለመስጠት በዚህ ፕሮግራም የተዘጋጀውን ስልጠና ያጠናቀቁ መምህራንን በማሰማራት ዲጂታል ኮርስ ይዘቶችን በማደባለቅ መስጠት እንዲጀመር እንዲሁም ለተማሪዎቹ የተዘጋጁ የክህሎት ማጎልበቻ ኮርሶችን ለመስጠት እንዲረዳ፣

1. ለሁሉም ተማሪዎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የ"Student Success Suit (SSS)" ኮርሶችን ወስደው እንዲያጠናቅቁ ለማድረግ የሚያስችል የጊዜ ሰሌዳ (class schedule) ከመደበኛ ትምህርታቸው የጊዜ ሰሌዳ ጋር ተካቶ እንዲዘጋጅላቸው፣
2. ሁሉም ተማሪዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ወደ ኮምፒዩተር (computer lab) በመግባት ኮርሶቹን እንዲያጠናቅቁ፣
3. ኮርሱን ወስደው ያጠናቀቁ ተማሪዎችን ብዛት በጾታ እና በትምህርት ዓመት በመለየት መረጃ በማደራጀት እና
4. ኮርሱን ያልወሰዱ/ያላጠናቀቁ ተማሪዎችን ብዛት በጾታ እና በትምህርት ዓመት በመለየት ሪፖርት እንድታደርጉ አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ኮራ ጡሹኔ ጉዳና
ሚኒስትር ዴኤታ

**ግልባጭ**

ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ጽ/ቤት
ለአይሲቲና ዲጂታል ትምህርት መሪ ስራ አስፈጻሚ
ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ
**ትምህርት ሚኒስቴር**